# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 1-3 ልዩ እትም መስከረም / ህዳር 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ሥርጭቱን የጀመረው የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ የአራት ወራት የአገልግሉት ግዜውን አጠናቅቆ አምስተኛ ውን ወር ሊይዝ ነው።

የቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎች ፤ ትችቶችና ትንተናዎች ፤ ቃለ መጠይቆች ወዘተ በአየር ላይ ውለው ሳይጨበጡ እንደተበተኑ የትም እንዳይቀሩና በፅሁፍ ተቀርፀው ቢቀመጡ ለተደራሲው የሚሰ ጡት ጥቅም የላቀ ይሆናል ብለን በማሰ ብ ፤ ከወራት በፊት አንድ መፅሄት ለመጀመር አቅደን ጊዜ ጊዜን እየወለደ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

ባለፉት አራት ወራት ቀስተ ደመና ሬዲዮ ያስተላለፋቸውን ትችቶችና አስተያየቶች በማቀናበር ይህንን 'ልዩ እትም' አዘጋጅተናል። የተለያዩ ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት እነዚህ አስተያየቶች በርካታ ቁም ነገሮች ያስጨብጣሉ የሚል ዕምነት አለን።

የ 'ቀስተ ደመና' ጋዜጣ ከዚህ ልዩ እትም በኋላ በየግዜው እንደሚወጣ ልናበስር እንወዳለን።

መልካም ንባብ !

ቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚተላለፍበት ፕሮግራም ገጽ......................................19

* የኢሃደግን ጦር ጠማሽ አቋም ላለማገዝ...........
ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ......................................4

* የቡድን ውኹንብር ጠቃሚነቱ ለአምባገነኖች ብቻ ነው ...............10

* ከፓሪሱ ጉባዔ ያልተቀሰመው ትምህርት..................................3

* ከዶላር ወይስ ከናቅፋ ከጽድቅ ወይስ ከኩነኔ.....................9

* ለብቸኛው ልዕለ ኃያል የሚሳነው ነገር አለ ለካ ሄ ሄ.....13

* በነ ዶር ታዬ ላይ በሃሰ ት አልመሰክርም በማለት ራሳቸው በሃሰት የተወነጀሉት ....................15

* ከባሻገሩ ሽግግሩ እንዳያስቸግር..18

* ለነፃ ምርጫ አመች የኃይል ሚዛን መታገል አንገብጋቢ ጥያቄ ነው .............................................6

አስተያየት፤ ትችት፤ ወዘተ ካላችሁ አድራሻችን እንደሚከተለው ነው፤
Radio Rainbow
c/o P.O.Box 140104
53056 Bonn , Germany . Fax : 0049 228 612381

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la pain en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

ድረስ ያይል ይስፋፋ የምንለው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ምን ያህል ያቀበትና የመስዋእትነት ጉዞ እንደሆነ እናውቃለን

ዛሬ በትጥቁም ሆነ በሰላማዊው ትግል መስክ ይህ መስዋእትነት እየተከፈለ ነው። የዚህን መስዋእትነት እድሜ ማሳጠርም ሆነ ፍሪያማነት ለማረጋገጥ የሚቻለው በአንድ ዘዴ ብቻ ነው። ተቃዋሚ ኃይሎች የዛሬ አራት አመት ይዘውት የነበረውን የፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ አጥቂነት እንደገና በጋራ ለመጎናፀፍ የሚችሉበትን ዘዴ መሻት አለባቸው። ለዚህ መንደርደርያ የሚሆን ባለፍው ዝግጅታችን የጠቆምነው የፓሪሱ 7 ድርጅቶች የተስማሙበት በኋላም የአዲስ አበባው ጉባኤ የተቀበለው
አታጋይ ሰነድ አለ። በዚህ ሰነድ መንደርደርያነት በድርጅቶች መሃከል በተለይ ደግሞ በየድርጅቶቹ አባላት መሃከል ውይይት እንዲካሄድ ፤ ከዚያም አልፎ የትግሉ አንድነት ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ዜጎች በሙሉ እንዲመረምሩት ከሚቀጥለው ዝግጅታችን ጀምረን ለአድማጮቻችን እናቀርበዋለን።

## ለነፃ ምርጫ አመች የኃይል ሚዛን መታገል ዛሬም አንገብጋቢ ጥያቄ ነው

መስከረም 29 ÷ 1990

ባለፈው ዝግጅታችን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ከ 4 ዓመታት በፊት በጋራ ይዘውት የነበረውን የፖለቲካና የዲፕሎማሲ የበላይነት በማጣታቸው ሃገሪቱ፣ ህዝቦቿና ታጋይ ኃይሎቿ ለኢህአዴግ ብቻ የሚያግዝ ከፍተኛና አደገኛ ውዥንብር ውስጥ መውደቃቸውን ጠቁመናል ። በሌላ ዝግጅታችን ደግሞ በጋራ ይዘው የነበረውን የበላይነት በገዛ እጃቸው ከሰደዱ በኋላ መልሰው ለመጎናፀፍ በየግላቸው የማሳደድ ተግባር የትም እንደማያደርሳቸው ለማስገንዘብ ሞክረናል። በዚህ ዝግጅታችን ለዚህ ችግር ዋና ምክንያት የጋራና አታጋይ መድረክ መጥፋት እንዳይደለ አውስተን የፓርሱ 7 ድርጅቶች፣

1ኛ ስለሽግግሩ ዴሞክራሲያዊ ሂደት
2ኛ ስለሽግግሩና የህገ መንግሥት ጥያቄ
3ኛ ስለብሄሮች መብትና የኢትዮጵያ አንድነትና የልእልናዋ ጉዳይ
4ኛ ስለሰላምና ዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች የትግል ትብብር ጉዳይ

ተወያይተው የተስማሙበትን ሰነድ መልሰን ለውይይት ለማቅረብ ቃል ገብተን ነበር።

በዚህም መሠረት በዛሬው ዝግጅታችን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በምን ÷ወሳኝ ጥያቄ÷ ዙሪያ በጋራ መቆምና መታገል እንዳለባቸው ፤ ይህንን ትግልም ለማስተባበር መፈጠር ስላለበት አካል ያሰፈሩትን ካቀረብን በኋላ አስተያየታችንን ለሰባቱ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት፣ ከነሰ -ም ባሻገር በሚሊዮን ለሚቆጠሩት ታጋይ ዜጎችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እናቀርባለን።

በዚህ ጥያቄ ላይ ሰባቱ ድርጅቶች ያሰፈሩት ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ነው።

### የሰላምና ዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች የትግል ትብብር ጥያቄ

በኢትዮጵያ ሰላም ወርዶ ዘላቂ እንዲሆን ፤ የዴሞክራሲ መሰረት ተጥሎ በሱ ላይ አዲስ ስርዓት እንዲገነባ ለሕብረተሰቡ መሰረታዊ ችግሮች አማራጭ መፍትሄዎች አቅርቦ በዴሞክራሲያዊ ምርጫና በህዝብ ድጋፍ ከሥራ ላይ ለማዋል ሰፋ ያለ ውክልና ያለው መንግስት በአገሪቱ ዛሬ የለም።

ያለው የሽግግር መንግስት ህብረተሰቡን እንደትና ወደት እንደሚሸጋገር እሱው በመሰለው ወስኖ ተቃዋሚ ሃይ። ሉችን በማከሰም የራሱን ብቸኛ ስልጣን በመገንባት ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የሰላምና የደሞክራሲ ኃይሉች ግልጽ የሆነ አማራጭ በጋራ ለህዝቡ ገና አላቀረቡም ። ከዚህ ችግር የኢህአደግን ጸረ ደሞክራሲና ጸረ ሰላም አቋሞች እንደአመጣጣቸው ተራ በተራና በተበታተነ ሁኔታ በማውገዝ ብቻ መውጥት አይቻልም ። ለኢህአደግ ብቸኛ ስልጣን አማራጭ የሚሆን የጋራ የሽግግር ወቅት መድረክ ቀይሶ ለዚህ ተግባራዊነት በጋራ መታገልም አስፈላጊነቱና ወቅታዊነቱ ግልጽ ነው።

እንደዚህ ያለው አማራጭ የሽግግሩንና የሰላም ግንባታውን ሂደት አስመልክተን ከፍ ብለን በጠቀስናቸው መርሆዎች ላይ ሊገነባ ይችላል። የሰላምና ደሞክራሲ አማራጭ ዛሬ ማተኮር ያለብት የሚችለውም በሽግግሩ ዘመን የሰው ልጅ መብትና የህዝብቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እንዲከበሩ ፤ ደሞክራሲ እንዲሰፍንና በዚህ ደሞክራሲም ተግባራዊነት ነፃና ርዕታዊ ምርጫ ተደርጎ ሕገ መንግሥት አውጭ ምክር በት እንዲሰየም በሚደረገው ትግል ላይ ነው ።

የሰላምና ደሞክራሲ አማራጭ ኃይሉች ትብብር አላማ እንደዚህ ግልዕና ውሱን ስለሆነ ቀላል ሊመስል ይችላል ። ነገር ግን ያለው መንግስት ለሱ በሚያመቸው ሥርዓት ለመሸጋገር የሚችለው ቀስ በቀስ ጸረ ደሞክራሲን ለማንገስና በተቸበረበረ ምርጫ ብቻ በመሆኑ ይህ ጥያቄ ለሱን ሆነ ለሰላምና ደሞክራሲ ኃይሉች የሞት ሽረት ጥያቄ እንደሆነና ከግዘ ጋርም አንገብጋቢነቱ ይበልጥ እየጎላ እንደሚሄድ ለማንም ግልፅ መሆን አለበት። ከወዲሁ የዚህ ጥያቄን ወሳኝነት ተረድቶ መንቀሳቀስ ለመጭው ትግል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

አንደኛ የሰላምና ደሞክራሲ ኃይሉች ከሽግግሩ ባሻገር በምትመሰረተዋ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ፤ የፖለቲካና የማህበራዊ ተቋሞች በምያዋቅረው ህገመንግሥት ላይ ያሉዋቸውን ልዩነቶች ለህዝብ ደሞክራሲያዊ ምርጫ ትተው ዛሬ ከፊታቸው በተደቀነው እጅግ ከባድና ውስብስብ የሽግግር ወቅት ተግባር እንድያተኩሩ ይረዳል።

ሁለተኛ ኢሃአዴግ በአንድ በኩል ደሞክራሲና ነጻ ምርጫ ለህልውናው ጠር መሆናቸውን እያወቀ በለላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦችንም ሆነ የአለም አቀፍን ኮሙኒቲ ለማደናገር ለደሞክራሲና ለነጻ ምርጫ እንደቆመ ለማስመሰል ያላሰለሰ ሙከራ ያደርጋል። በመሆኑም የሰላምና ደሞክራሲ ኃይሉችን ትግል ከአሸዋ በበዙ ሰበቦች፤ ምክንያቶች፤ ሽፋኖችና መከራከሪያዎች እየተጠቀመ ለማደናገርና በዚህም ሃገሪቱን ወደ ጦርነትና ወደ ውዥንብር ይዞ ለመንጎድ የጀመረውን ሂደት እንደሚገፋበት ግልስ ነው። የሰላምና ደሞክራሲ ኃይሉች ይህንን የውዥንብርና የማደናገር ዘመቻ ሊቋቋሙ የሚችሉት እነሱም ለግዜው አንገብጋቢ ባልሆኑ ጥያቄዎች ላይ በማተኮር ሳይሆን በኢትዮጵያ ሕዝቦችም ሆነ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲ ፊት ይህን ወሳኝ ጥያቄ በጋራ ይዘው ሲቀርቡ ነው።

ይህንን ዓላማ በሥራ ላይ ለማዋልና ሌሉችንም የሃገር አቀፍ ሰላምና እርቅ ጉባዔውን ውሳኔዎች ለመከታተል የሚያስሽል ውክልና ያለው አካል ማቋቋም ከግዜው ዋና ተግባሮች ተቀዳሚ ይመስለናል። ይህ አካል ጉባዔው የወሰዳቸውን አቋሞች በተግባር ለመተርጎም በፖለቲካ፤ በዲፕሎማሲ ፤ በቅስቀሳና በለሉችም መስኮች የተሳታፊ ድርጅቶችን ትግል የሚያስተባብር አካል ይሆናል። የዓላማው መሳካት ለሽግግሩ ሂደት ሆነ ለሃገሪቱ የወደፊት እድል ወሳኝ ቢሆንም በዚህ አካል ትከሻ ላይ የሚጣለው አደራ ውሱንና ግዚያዊ በመሆኑ አሰራሩ በሁለት መሰረታዊ መርሆዎች ላይ መመርኮዝ ይኖርበታል ።

አንደኛ ከፍ ብሉ ለተጠቀሰው ዓላማ መሳካት በየግዜው አስፈላጊ የሚመስሉትን የትግል ስልቶች የማቀነባበር ኃላፊነት የሚኖረውን ያህል በአባል ድርጅቶች መሃል ስምምነት ባልተደረሰባቸውና አከራካሪና ከፋፋይ ሊሆኑ የሚችሉ ነጥቦች ላይ አቋምም እርምጃዎችም ከመውሰድ መቆጠብ ይኖርበታል።

ሁለተኛ ይህ አካል በውስን ዓላማ ላይ የተገነባ ግዚያዊ አካል በመሆኑ የአባል ድርጅቶች ያላቸውንና የሚያስፈልጋቸውን የድርጅት ነጻነትም ሆነ የፖለቲካ አቋምና የትግል ስልት ምርቻቸውን የሚነካ መሆን የለበትም።

ሰባቱ ድርጅቶች በውቅቱ የተስማሙት በነዚህ ነጥቦች ነበር። እንግዲህ እኛ ብቻ ሳንሆን አድማጮቻችን በሙሉ ያነሳሉ የምንላቸውን ጥያቄዎች ከራሳችን አስተያየት ጋር እያቀረብን አድማጮቻችን በዚህ ላይ የራሳቸውን አስተያየት እንዲልኩልን እናሳስባለን።

1ኛ ጥያቄ ። እነዚህ ቃላት ከተጻፉ አራት አመታቸው ነው ። ከዚያ ወዲህ የሽግግሩ ዘመን ያለቀ ስለሆነ አሁን ግዜው ያለፈባቸው አይደሉም ወይ?

መልሳችን በፍጹም አይደሉም። ሲሆን ተደረገ የተባለውን ሽግግር ምንነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማተት ለቀባሪው አረዱት ይሆኒብናልና ይህንን ትተን ሰባቱ ድርጅቶች ይመኙት የነበረውና ያልተሳከው ሽግግር ምን አይነት እንደነበረ በመጠቆም ብቻ እነዚህ ቃላት ዛሬም ምን ያህል አንገብጋቢና ወቅታዊ ተግባር እንደሚጠቁሙ ማሳየት እንሞክራለን።

ዛሬ ኢትዮጵያ የምያስፈልጋትና ህዝቦችዋም በጉጉት የሚጠብቁት ሽግግር አንድ መንግስት ለላውን የሚተካበት ፤ አንድ የፖለቲካ ሃይል በለላው የሚለወጥበት ወይም ደግሞ አንድ ግዚያዊ መንግሥት ወደ ቋሚነት የሚሸጋገርበት ሂደት ብቻ አይደለም።

የሚያስፈልገን ህብረተሰቡ በሙሉ ከአንድ ጸረ ደሞክራሲያዊ ሥርአት ወደ ተሻለና የመላውን ህዝብ ተቀባይነት ወዳገኘ ሥርአት የምንሄድበት ሽግግር ነው። በሁለቱ አስተሳሰቦች መሃከል ይህ ነው የማይባል ልዩነት አለ። በጸረ ደሞክራሲያዊ ሂደት፤ በይስሙላ ህገ መንግሥት ፤ በተጭበረበረ ምርጫ ዞሮ ዞሮ ደግሞ ይህንን ሁሉ በግዝያዊ ወታደራዊ የበላይነት አስመርኩዞ አንድ ግዚያዊ መንግሥት ራሱን ወደ ቋሚነት ልያሸጋግር ይችላል። ህብረተሰቡን ሳይዝ። ብቻውን።

ይህ ግን ኢትዮጵያ ካለፈው በሃይል የበላይነት ብቻ ከፈለቀ ጸረ ሰላምና ጸረ ደሞክራሰ ሥርአት ወደ አዲስ ስራት ተሸጋግራለች ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ያለ ደሞክራሲያዊ ሂደት ወደ ደሞክራሲያዊ ሥርአት መሸጋገር ይቻላል ማለት ዘበት ነውና።
"አጫፋሪና ጥቃቅን የሆኑ ሌሎች ክስተቶችን ወደ ጎን ብንተዋቸው ዛሬ በህብረተሰቡ ፊት የተደቀኑት ሁለት መሰረታዊ አማራጮች እነዚህ ብቻ ናቸው።" ብለው ሰባቱ ድርጅቶች ያሰ ፈሯቸውን ስናጤን ዛሬም ገና ደሞክራሲያዊ ሽግግር እንዳልተደረገና የነጻ ምርጫና የደሞክራሰ ያዊ ህገ መንግሥት ጥያቄዎች ወቅታዊ መሆናቸውን እናያለን።

ሁለተኛ ጥያቄ፤ ሰባቱ ድርጅቶች የነጻ ምርጫን ጉዳይ እንደ የጋራ አጣዳፊ ጥያቄ የወሰዱት በውቅቱ ኢህአደግ የህገ መንግሥት ጉባዔ ምርጫ በወራት ውስጥ ለማዘጋጀት ላይ እታች ይልበትና የአለም አቀፍም ኮሙኒቲ በዚህ ዙርያ አይኑን ያተኮረብት ወቅት ነበር ። ዛሬ ምርጫ የሚሉ ነገር ገና ከሶስት አመት በኋላ በሆነበት ወቅት ጥያቄው በአንገብጋቢነት የሚቀርብበት ምን ምክንያት አለ?
ለዚህ የመጀመሪያ መልሳችን አጭር ነው። እስኪ የኢትዮጵያ ታጋይ ኀይሎች ከለመዱት የሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ባህላቸው ተላቀው የሁለት ሶስት ዓመታት እፍታ ፤ አቅድ፤ ፕላንና ራእይ ያለው ሥራ ይሥሩ የሚል መልስ ነው።
ሁለተኛም ጉዳይ አለ። ገና ግዜ አለ ብሎ መዘናጋት ስለምርጫ የተሳሳተ አስተሳሰብን ያንጸባርቃል። ነጻ ምርጫ ሲባል ከዚህ ቀደም በአንድ ዝግጅታችን እንዳልነው ለደሞክራሲያዊ ኀይሎች አመዛኝ የሆነ የኃይል ሚዛን ከወዲሁ መፍጠርን ይጠይቃል። ይህ ደግሞ እንኳን በተናጠል ቀርቶ በጋራ ሆነን ብንያያዘው እንክዋን ልዥምና እልህ አስጨራሽ ትግል ስለሆነ ሶስት አመት የሚበዛበት አይደለም።

ሶስተኛ ጥያቄ ። የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ በተለይም ደግሞ ምእራባውያን የኢህአደግን መንግሥት ደሞክራሲያዊ ብለው ካሞከሹት በኋላና በሃገሪቱም የተደረገውን ምርጫም አንዳንዶቹ ነፃና ርዕታዊ ብለው ከተቀበሉት በኋላ ይህ ነጻ ምርጫና ደሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት የሚለው የትግል ጥሪ አሁንም ለዲፕሎማሲ ትግል ወሳኝነት አለው ወይ የሚለው ጥያቄ አለ። እኛ አለው እንላለን።

ኢህአደግ ከነዛ ጥላው ጋር በተወዳደረበት የምርጫ ሂደት በራሱ ላይ ያዳላ አያዳላ እንደሆነ ለመታዘብ ተቋቁመው ራሳቸውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትዝብት የዳረጉት ባእዳን ታዛቢዎች ባቀረቡት ሪፖርት መጨረሻ ላይ "ምርጫ ማለት የሚመረጥ ነገር ሲኖር ነው።

በአሁኑ ምርጫ የተለየ አማራጭ ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች አልተሳተፉም። ይህ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ የተወሰነ ይሆናል።" ብለው ደምድመዋል።

ይህም በመሆኑ ነፃ ምርጫ ሲሉ እነሱም እንደኛው ከልባቸው ከሆነ በተጨባጭ በዚህ ጉዳይ ዓለም አቀፍ መርህዎችና ሰነዶችን ከኢህአደግ ሂደት ጋር እያነጻጸርን ፤ ቅራኔዎችን እየጠቆምን ወይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ ወይ ደግሞ "ያለው ይበቃችኋል" ብለው እቅጩን ነግረውን ይህንኑ ደሞክራሲያዊ ህልማችንን ይዘን በይህዝቦቻቸው ፊት እነሱንም የማንታገልበት ምን ምክንያት አለ።

<u>አራተኛ ጥያቄ</u>። ዛሬ ለደሞክራሲ የሚታገሉ ኃይሎች በህጋዊ ዘዴ ሆነ በህገወጥ መንገድ፤ ከኢህአደግ ውጭ ሆነ ኢህአደግ ውስጥም በውስጥ አርበኝነት፤ በይፋ ሆነ በህቡዕ ፤ በትጥቅ ሆነ በሰላማዊ ትግል መስከ ተሰማርተው ይገኛሉ። ይህ መሰበጣጠር ለጋራ ትግል አይሆንም ወይ? የሚለው ጥያቄ አለ። የኛ መልስ አያሸግርም የሚል ነው።

መጀመሪያ ነገር አንድ መሠረታዊ ሃቅ አለ። እርግጥ በተሰበጣጠረ የትግል ስልት መሰ ማራት አንዳንድ ታጋዮችን የጋራ የሆነ የዘላቂ ሰላምና የአስተማማኝ ደሞክራሲ ዓላማ እንዳለ ሊያስረሳቸው ይችላል። ነገር ግን ለእንደዚህ አይነቶቹ ዜጎች ያለን መልእክት ግልጽ ነው። በትግል ስልት ልዩነት የተነሳ የጋራ አላማ መሳትን የመሰለ ለክፍፍልና ለጋራ ሽንፈት ንጣፍ የሚሆን እንቅፋት እንደሌለ በገዛ የትግል ታሪካችን ደጋግመን ዓይተነዋልና ከዚያ ትምህርት ይቅሰሙ እንላለን።

ሁለተኛም ጉዳይ አለ። የፓሪሱ ሰባት ድርጅቶች በዚህ ሰነድ ሲስማሙና የትግል አንድነታችንን የሚያስተባብር አንድ አካል ይኑረን ሲሉ ሁሉም በአንድ አይነት የትግል ስልት የተሰማሩ እንዳልነበሩ የታወቀ ነው።

ሶስተኛ ነገር ይኸው ጥያቄ በዚሁ ሰነድ ላይ ግልጽ መልስ አግኝቷል። ሰባቱ ድርጅቶች ለጋራ ትግል አንድ የጋራ አካል እንፍጠር ሲሉ ይህ አካል የአባል ድርጅቶችን የፖለቲካ አቋም ፤ ድርጅታዊ ነጻነትና የትግል ስልት ምርጫ የማይነካ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጠዋል።

ባጭሩ በኛ አስተሳሰብ ሰባቱ ድርጅቶችና ሌሎችም ድርጅቶች ልዩ የፖለቲካ አቋማቸው ፤ ድርጅታዊ ነጻነታቸውና የትግል ስልት ምርጫቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የዛሬ 4 ዓመት እንገብጋቢ ብለው ባስቀመጡት ጥያቄ ዙሪያ የማይተባበሩበትና ያጡትን የፖለቲካ የበላይነት ለመያዝ ለመታገል የሚከለክላቸው ምንም ምክንያት የለም። ከነዚህ ድርጅቶች ባሻገር የሰላምና የእርቅ ጉባዔውን ለመደገፍ በሃገር ውስጥ ተንቀሳቅሶ የነበረው በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ፤ ለዚህ አላማ ከሰሜን አማሪካ
እስከ አውስትራሊያ ድረስ በኮሚቴ እየተደራጁ ለጉባዔው መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት ወገኖቻችን ዛሬ ለዚህ ሕዝባዊና ደሞክራሲያዊ ዓላማ እንደገና የማይንቀሳቀሱበት ምን ምክንያት አላቸው? ////

## ከዶላር ወይስ ከናቅፋ ? ከጽድቅ ወይስ ከኩነኔ ?

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የሚካሄደው ንግድ በዶላርና በሌላ የውጭ ምንዛሪ እንዲሆን መወሰኑ የነመለስ ዜናዊና የሌሎች ለሻብያ አጎብዳጅ ባለሥልጣኖች ውሳኔ ባይገባበትና ባያዘባርቀው ኖሮ ይህ ፖሊሲ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስቀድም ነበር። ይህ ፖሊሲ ትክክል ነበር የምንለው ናቅፋ የተባለውን ገንዘብ ልክ እንደ ሃገራችን ብር በኢትዮጵያ እንዲገባ ማድረግ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆኑ በመገንዘብ ነው።

አንደኛ፤ በብርም በናቅፋም እኩል መገበያየት ቢቻል የሻቢያ ነጋደዎች ከኢትዮጵያ የሚያስፈልጋቸውን በዶላር ሳይሆን በናቅፋ ይገዛሉ። እነዚህን ሸቀጦች የኢትዮጵያ ነጋደዎች በዶላር ሊሸጡ ሲችሉ በናቅፋ እየተሸጡ የኤርትራ ነጋደዎች ደግሞ መልሰው በዶላር ሊሸጧቸው ይችላሉ። ማለትም እኛ ናቅፋ ታቅፈን እነሱ በኛው ሸቀጥ ዶላር ያካብታሉ ማለት ነው። ባጭሩ ኢትዮጵያ በዛሬው ወቅት ጥቅሟን የሚያስቀድምላት ሃላፊነት የሚሰማው መንግሥት ባለመታደሏ ከዶላር ይልቅ ናቅፋን ፤ ከጽድቅ ይልቅ ኩነኔን መረጠች የምትባልበት አስገራሚ ሁኔታ ውቅን ማለት ነው።